

# ☙ 3 ❧

# በፈተና መጽናት እንዴት ይቻላል?

## 3-1

ባለፈው የሕይወት መስታወት እትማችን ክርስቲያን የሚያቋርጥ ፈተና እንደሚያጋጥመው በመጠኑ ተልጿል። አማኝ ፈተና በየጊዜው እንደሚደርስበት ይወቅ እንጂ፥ እንዴት አሸናፊ መሆን እንደሚችል ግን የሚገባውን ያህል አያውቅም። በዚህ ጽሁፋችን ካለፈው ትምህርት በመቀጠል ክርስቲያን በፈተናው አሸናፊ መሆን የሚችልባቸውን ሃሳቦች በመጠኑም ቢሆን ለመስጠት ሞክረናል። አማኝ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ሙሉ በሙሉ ሕይወቱን የሰጠና እንዲሁም ከአምላኩ ጋር በታማኝነት ለመራመድ ቃል ኪዳን የገባ ነው። ያንንም የገባውን ቃል ኪዳን በታማኝነት መጠበቁን ማስመስከር የሚችለው በየጊዜው ከመስመር እንዲወጣ የተለያየ ግፊት ሲደርስበት ከመስመር ሳይወጣ ጸንቶ የቆመ እንደሆነ ብቻ ነው። በሁለት ሰዎች መካከል የተመሠረተው ፍቅርና ኅብረት የሚመዘነው በመካከላችው የቆመው ቃል ኪዳን ሳይፈርስ ተጠብቆ የቆመ እንደሆነ ነው። እንዲሁም ሰው ከክርስቶስ ጋር የሚኖረው ኅብረትና ፍቅር የሚለካው ለአምላኩ የገባውን ቃል ኪዳን ያላፈረሰ እንደሆነ ብቻ ነው። አማኝ ፊቱን ከእግዚአብሔር እንዲያዞር በየጊዜው ግፊት ይደርስበታል። ብዙ ጊዜ በግፊቶቹ ምክንያት ከመስመሩ ባይወጣም፥ አልፎ አልፎ ግን መሰናከሉ አይቀርም። ጉልበቱ ተጠናክሮ መራመድ ከዚያም መሮጥ ከመቻሉ በፊት ህጻን ልጅ ብዙ ጊዜ እየወደቀ እንደሚነሳው ሁሉ፥ አማኝም በክርስትና ህይወቱ እስከሚጠናከር ድረስ ብዙ ጊዜ በመንገዱ መውደቅና መነሳት ይደርስ በታል። አማኝ በፈተናዎቹ ላይ ድል ማግኘት የሚችልባቸውን መንገዶች ከመመልከታችን በፊት በመጠኑም ቢሆን ፈተና ምን እንደሆነ እንመልከት።

## ፈተና ምንድነው?

የዌብስተር እንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት የፈተናን ትርጉም ሲሰጥ በሁለት ይከፍለዋል።

1. ፈተና ማለት የተፈታኙ ኃይል ወይንም ችሎታ መመዘኛ መንገድ ነው ሲለው፥
2. ተፈታኙን በማባበል ወይንም በማግባባት ከመስመር ማስወጫ መንገድ ነው ይለዋል።

ሀ) ማንኛውም ሰው ትክክል የሆነና ያልሆነ ሁለት አማራጭ መንግዶች ይቀርብለታል (Confrontation)

ለ) ከቀርቡለት ምርጫዎች መካከል ትክክል ያልሆነውን መንገድ እንዲመርጥ በልዩ ልዩ ዓይነት ጥበብና ዘዴ ሙከር ይደርግበታል (Test)

ሐ) ሰው ከቀረቡለት ሁለት ምርጫዎች አንደኛውን መርጦ መያዝ ሲያቅተውና ሁለቱንም መያዝ

ሲሞክር በውስጡ ደስ የማይል ከፍተኛ ትግልና ግጭት መፈጠሩ ግልጽ ነው (Conflict)። ማንኛውም ሰው ሁለት አማራጭ መንገድ ስላለው ካሉት ሁለት ምርጫዎች አንዱን ይመርጥና ሁለተኛውን ይጥላል። ውስጣዊ ትግሉ ብርቱ የሚሆነው ከሁለቱ አማራጭ ውሳኔዎች አንደኛውን ለመምረጥ ጉዳቱንና ጥቅምን በአዕምሮው በሚመዝንበት ወቅት ነው።

## ፈተና በሁሉም ይደርሳል

ብዙ ክርስቲያኖች “በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላሁ ለምን እፈተናለሁ?” በማለት ይጠይቃሉ። በመሠረቱ ፈተና ከሰው ተፈጥሮአዊ ፍላጎት የተነሳ ከመምጣቱም በላይ፥ በኃጢአት ወይንም በጽድቅ መንገድ የመራ መድ ምርጫ ኖሮት ከሁለት አንዱን ሲመርጥ ነው። ሰው በሚመርጠው ምርጫ ምክንያት እግዚአብሔር የሚከብር ከሆነ፥ ምርጫው ያለ አንዳች ተጽኖ በራሱ ውሳኔ ብቻ መሆን አለበት። ሰው ከደግ ይልቅ ክፉውን የመምረጥ ዝንባሌ እንዳለው እግዚአብሔር ቢያውቅም የመምረጥ መብቱን እንዲወስድበት አልፈለገም። በአማኝም ሕይወት ፈተና እንዲመጣ የሆነው፥ ፈተና ዶርሶበት ካልታየ በስተቀር ታማኝነቱና ታዛዥነቱን የሚያረጋግጥበት መንገድ ስለሌለ ነው። ማንኛውም ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላም ቢሆንም ኃጢአት የመሥራት ዝንባሌ አለው። ይሁን እንጂ ኃጢአትን ለመቃወም ሁሉም ክርስቲያን ተመሳሳይ አቅም አለው ማለት አይደለም። ስለሆነም ሰይጣን ፈተናውን የሚዘረጋው አማኙ የሚደክም በትን አቅጣጫ እየተመለከተ ነው። መቼና በምን እንደሚፈትነው ጠንቅቆ ያውቃል።

## መፈተን ኃጢአት አይደለም

ብዙ ክርስቲያኖች አሸናፊ ሕይወት እንዳይኖራቸው እንቅፋት ከሚሆንባቸው መካከል አንደኛው ትንሽም ሆነ ትልቅ ሃሳብ ወደ አእምሮአቸው ከመጣ ገና በደሙ ያልነጹ ኃጢአቶች እንደሆኑ መስሎ ስለሚ ታያቸው ነው። በዚህም ምክንያት በፍርሃትና በስጋት ዘመናቸውን ያሳልፋሉ። በመሠረቱ መፈተን ኃጢአት አይደለም። ክርስቶስ ተፈትኖአል፤ ሆኖም ኃጢአት ሠርቶአል ማለት አይደለም። ኃጢአት የሚሆነው ለፈተናው እጃችንን የሰጠን እንደሆነ ነው (ያዕ. 1፥14-15)። ያም ሆኖ እግዚአብሔር ልጆቹ ከፈተና ነጻ ሆነው እንዲኖሩ አይፈቅድም (መ. ዜና መዋዕል ቀዳ. 29፥17)።

## ፈተና አቋማችንን ይለካል

ፈተና ለክርስትና ሕይወታችን አስፈላጊ ነው (ያዕ. 1፥2-4)፣ (ሮሜ 5፥3-5)። እግዚአብሔር ልጆቹ ከፈተና ነጻ ሆነው እንዲኖሩ ባይፈቅድም፥ በሚያጋጥማቸው ፈተናና ትግል ውስጥ ግን አሸናፊና ብርቱ ሆነው እንዲወጡ ይፈልጋል። በእርሱ ፍቅርና ኃይል እንዲታመኑ ይነግራቸዋል (ሮሜ 8፥28)። የመፈተና ችን ዋና ዓላማው እኛን ተስፋ ለማስቆረጥ ወይንም ለመጣል የሚዘረጋ ወጥመድ ሳይሆን ለመንፈሳዊ ዕድገ ታችን አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

**በሚቀጥለው ክፍል፥ ሦስት ዓይነት የፈተና ደርጃዎች እንመለከታለን።**

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን!**